# ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር

ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል (፪)
መታመኛዬ እርሱ ነውና ይገባዋል ክብርና ምስጋና

ክብሩን እያሰብን እንቅረብ ወደ እርሱ
ይምረናልና መሃሪ ነው እሱ
በልባችን ይንገስ ይግባ ከቤታችን
የሕይወታችን ዋልታ እርሱ ነው ተስፋችን (፪)

አዝ...

ከቶ አላገኘም እርሱን የሚመስል
ነፍሴን የሚያከብራት የሚሰጠኝ ኃይል
በመከራ ሠደት ከክፉ የሚያድነኝ
ከዬት አገኛለሁ መጠጊያ የሚሆነኝ (፪)

አዝ...

የለመለመ መስክ መሸሸጊያዬ ነው
በሰላም ወጥቼ ሠላም እገባለሁ
ተስፋዬ እርሱ ነው ይጠራኛልና
ዘወትር አቀርባለሁ ክብርና ምስጋና
ዘወትር አቀርባለሁ ለአምላኬ ምስጋና (፪)

አዝ...

እኔስ ይሻለኛል መቅረብ ወደ ጌታ
ጋሻዬ ነውና የነፍሴ አለኝታ
ስለዚህ እቀርባለሁ አልርቅም ከደጁ
ጠግቤ እኖራለሁ ከበረከት እጁ (2)

አዝ...